
መቁጠርያ

t.me/abat_memhir_girma





※ **መቁጠርያ** ፤ ማለት ትርጒሙ ጐለቄ (ቈጠረ) ካለው የግእዝ ግስ የወጣ ሲሆን፣ ፩፣ ፪ አያኩ መቍጠር፣ አቈጣጠር፤ ቈጠራ ማለት ሲሆን ዋና አገልግሎቱ በየጸሎት ጊዜያት ለመጸለያነት ነው አባቶቻችን የሚጠቀሙበት።

※ ምሳሌነቱም፤ መድኀኔ ዓለም ክርስቶስ የተገረፈበት ልምጭን በማሰብ በአብ መልክ ተቀርጾ ÷ በገመድ ውስጥ ገብቶ የምንጠቀምበት ነው።

♦በጥንታዊቷ ቤተክርስቲያናችን ከሚገኙና ሰይጣን ዲያብሎስን ከምንዋጋበት መሣሪያዎቻችን መሳሰል አንዱ መቁጠሪያ ነው ፡

"በአንተ ጠላቶቻችን እንወጋቸዋለን በስምህም በላያችን የቆሙትን እናዋርዳቸዋለን " መዝ.43 (44)÷5

መቁጠሪያ በአምልኮ ሕይወት ከመገልገያ ቁሶች አንዱ ነው። ከዛሬ መቶ ሃያ አመት በፊት የነበሩ አባቶች በኃይለ ጸሎት አጋንንትን አሥረው በመቁጠሪያ በመቀጥቀጥ ድል ይነሡ፤ ሥጋቸውንም ከነፍሳቸው ያስገዙበት ነበር። አሁንማ የቀደመ ግብሩ ተረስቶ "መቁጠሪያ ከቆራቢ ነው፤ ከመነኮሱት ነው፤ ከባሕታውያን ነው።" መባሉ ትልቅ ስህተት ነው ።
በመጽሐፍ ቅዱስ 1ኛ ቆሮንቶስ 9÷27 ላይ ያለውን ቃል አንመልከት።
"ነገር ግን ለሌሎች ከሰበክሁ በኋላ ራሴ የተጣልሁ እንዳልሆን ሥጋዬን አየጎሰምሁ አስገዛዋለሁ።"
አየጎሰምሁ ሲል አየቀጠቀጥኩ ማለቱ ግልጽ ነው።

- በአጠረ አገላለፅ መቁጠሪያ መንፈሳዊ ካብራቶሪ ነው፤ ስውሩንና ውስጠኛውን ሕይወት መፈተሻ ። ይህን የመቁጠሪያን አገልግሎት ቀደምት በተለይም ከ60 ' ዎቹ ዘመን ቀድመው የነበሩት አባቶቻችን የአምነት ታሪክ አውነት ውስጥ ያለ የአግዚአብሔር ጦር ዕቃነቱ በተገባ ያውቁታል።
በመሠረቱ መ - ቁ - ጠ - ር - ያ ነው ራሱ ቃሉ። አባቶቻችን ቁጥር አንዳያገድፉ አግዚኦ መሐረነ ክርስቶስን ፣ በአንተ ማርያም መሐረነ ክርስቶስን ፣ ኪርካይሶንን ፤አ አምላክን፤ አ ክርስቶስን ፣ ያድኅነነ ከመባቱ ይሰውረነ በምሕረቱ በአንተ ማርያም ወካዱቱን ፤ ስምዓነ አምላክነን፣በስመ ምሕረትህ ወአኮ በስመ አበሳነ (አንደ ምሕረትህ አንጂ አንደ በደላችን አይሁን) ። ተዘክረነ አግዚኦ በውስተ መንግሥትህን 41ም ፣ 64ም ጊዜ፣ በመቁጠር ይማልዱበትም ነበር።

መቁጠርያን ሳመጠቀም ቢፈት

- ✔ ከተገዛ በኋላ በካህን ማስባረክ።
- ✔ ከጸሎት ቦታ ውጪ አለማስቀመጥ።
- ✔ 41 ወይም 64 የአምልኮ ይሰገድበታል።
- ✔ የዕለቱን ጸሎትና ምስጋና ካደረሱ በኋላ በስመ መለኮት መባረክ፡

- ❖ ቅዱስ ኤልሻዳይ
- ❖ ቅዱስ አዶናይ
- ❖ ቅዱስ ያሕዌ
- ❖ ቅዱስ ጸባኦት
- ❖ ቅዱስ ኢየሱስ
- ❖ ቅዱስ ክርስቶስ
- ❖ ቅዱስ አማኑኤል
- ❖ ቅዱስ ኢያኤል
- ❖ ቅዱስ ታዳኤል
- ❖ በአብ ፤ በወልድ ፤ በመንፈስ ቅዱስ ስም
- ❖ በቅድስት ሥላሴ ስም
- ❖ በጌታችን መድኃኒታችን በኢየሱስ መድኅነ ዓለም ክርስቶስ ስም
- ❖ በእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ስምና በቅዱሳን ስም ወዘተ..

የተባረከ ፣ የተቀደሰ ፣ በእግዚአብሔርም የተወደደ ፣ ኃይለ መለኮቱም ያረፈበት ፣ የጸጋውና ሞገሱ ክብር የተገለጠበት ፣ የዲያቢሎስንም ክንድ የሚሰበር ፣ሥራውንም የሚያፈርስ ይሁን።
ወስብሐት ለእግዚአብሔር፣ ወለወላዲቱ ድንግል፣ ወለመስቀሉ ክብር አሜን!!
በማለት መባረክና ጸሎት ቤት የሚቀመጥ ቅብዓ ዘይትን ካልተገኘ እምነት መቀባባት።

መቁጠሪያን እንዴት እንጠቀመበት?

አብዛኛውን መንፈስ የት የት ይቀመጣል የሚለዉን ስናስተውል

- ✔ ቀኝና ግራ ላይ ትከሻ፣
- ✔ ማጅራት አከባቢ በጀርባ አከርካሪ ፣
- ✔ ራስ እና ግንባር ላይ
- ✔ ዓይን፣ክንድ፣ እጅ፣ እግር ላይ ወደ ሌላ መንገድ ሊወስደንና ሊመራን ሲፈልግ እግር ላይ ነው የሚቀመጠው።
- ✔ በውሳጣዊ ባሕርይ ደግሞ ልብ፣ ሕሊና፣ አእምሮ ላይ ይቀመጣል፡
- ✔ በጸሎት ጊዜ ከኒህ ውጪ ባለ ክፍል ላይ ሲቀመጥ፤ ጸሎት ከሌለ ግን ሕሊና፣ አእምሮና፣ ልቦና ላይ ይደላደላል ። ሕሊና፣ አእምሮና ልቦናም ከነፍሳችን አንደኛው ክፍል ናቸው። እኒህን ተቆጣጠረ ማለት መቶ በመቶ ገዛ ማለት ነው። በአብዛኛው ልብ እና ሆድ ውስጥ በሚመታበት ግዜ መብላት፣ ማቃጠል፣ መውረር የተለየ ባሕርያቱና መገለጫው ነውና አድፍጦ፣ መሸጎአል ማለት ነው። ከዚያ ማዳከም ተከታይ ግብር ይሆናል። በጸሎት ቦታ ላይ፣በመዝለጥ ፣ ትዕዛዝ በመስጠት ማዳከም፣ በቅድስት ሥላሴ ስም አሥራሃለሁ አትረብሸኝ፤

በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አዝዣሀለሁ፤ በድንግል ማርያም ስም አዝዘሀለሁ በማለት በመቁጠርያ ሲመታ የፍርሃት ባሕሪ ይመጣል። ጫን ባለ ምት ሆድ አካባቢ፥ ግራና ቀኝ ትከሻ፣ በማጅራት አካባቢ ማፋፋም ፣ ራስ ላይ ሲቀወርና ግንባር ላይ ውጣ ሲባል ልክ እንደሚንቀሳቀስ ነፍሳት ሆኖ ወደ ግንባር ላይ ሲወጣም ሊሰማን ይችላል። እዚያው ማሠር። ግንባር ላይ መታሠሩ ለምንድነው? አሥረን ስንጸልይ፣ ስንሰግድ፣ የምናየውን እንዳያይና ማስተዋላችንን እንዳይጋርድ እንዘጋበታለን ። ከዓይን ፣ ከጀሮ ውጣና ታሠር ሲባል ግንባር ላይ ይታሠራል። አሁን ስንሰግድ አብሮ ይሰግዳል። አልሰግድም ብሎ የወደቀ መንፈስ ስለሆነ ይቃጠላል። በየጊዜው በመቁጠርያ እየቀጠቀጥን ስንለበልበው እየተዳከመ በልብ ውስጥ፣ በሕሊና ወይም በጀሮ በኩል መናገር ይጀምራል። ማን ምንድን ነህ ከየት ነህ የመጣኸው? የዘር ነህ?፣ የቤተሰብ ነህ? በምን ገባህ? ወዘተ.... ስትጠይቀው ለራስህ በውስጥህ ይነግርሃል ሌላ ጠያቂም አያስፈልግ።

መን መን እያልን እንቀጥቅጥ?

t.me/abat_memhir_girma

❖ ይህንን ለመመለስ ሕይወታችንን መቃኘት የግድ ነው። ከውስጥ ያደፈጠ ጠላት በሕይወታችን በምን መልኩ አጥቅቶናል? የሕይወታችን አኗኗር የቱ የቱ ላይ ተሰነካክለ? ምን ችግር ደረሰብን? የሚሉትን መሰል ጥያቄዎች አሰላስለን የመሸገውን ክፉ መንፈስ በቅዱስ ስሙ ኃይል መቀጥቀጥ ነው። ለምሳሌ

- ✓ **የቤተሰብ በዘር የተዋረስህ ዛር ፣ ጠቋር፣ ቡዳ ፣ መተት ፣ ዓይነጥላ፣ ሰለቢ ፣ ክፉ ኃይል፣ ጤናዬን የምትነካ ፣ ሰላሜን የምታውክ ፣ ችግር፣ ጭንቀት የሆንህ ፣ ደስታዬን የነጠቅህ ፣ ቤተሰቤን የበተንክ ፣ ራዕዬን የዘጋህ፣ ዕድሌን የቀማህ ፣ ትምህርቴን ያበላሸህ ፣ዕውቀቴን የገለበጥህ፣ ሥራዬን ያከሸፍህ ፣ ምቀኛ ጠላቴ የሆንህ፣ ባሕሪዬ የሆንህ፣ በውስጤ ያደፈጥህ ፣ በቤቴ ውስጥ የመሸግህ ፣ በቤተሰቤ ውስጥ የተደበቅህ . . .ወዘተረፈ**

የሥላሴ ስም ያንድድህ ፣ የኢየሱስ ክርስቶስ ስም ያሳድዱህ ፣ የአመቤታችን ወላዲተ አምላክ ስም ያቃጥልህ ፣ አንደሠርክኝ የኪቀ መልዐኩ ቅዱስ ሚካኤል ስም ይሠርህ ፣ አንደሰቃየክኝ የብሥራት መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ስም ስልጣንህን ይሻረው፣ በጸባኦት ፣ በአዶናይ ፣ በኤልሻዳይ ፣ በያህዌ ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ፣ በአማኑኤል በስመ መለኮት ያዳፈጥህ ሰይጣን ተቃጠል
በወላዲተ አምላክ ፣ በቤዛዊት ማሕም ፣ በቅድስት ኪዳነ ምሕረት ፣ በአናታችን ድንግል ማርያም ስምና ጸጋ የተደበቅህ አጋንንት፣ ሰይጣን፣ሥራህን ሁሉ አቁም። ሐሳቤ ውስጥ ሐሳብ የሆንክ ፣ አካላቴ ውስጥ አካል የሆንክ ፣ ተመሳስለክ ያደግህ አመል ጸባይ የሆንህ ጠላት፣ በመድኀኒተ ማሕም በአምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ ስም ግንባር ላይ ውጣና ታሠር፣ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም ተይዘሃል። በወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም ስም ታሠረሃል።

t.me/abat_memhir_girma

እንዲህ በማለት ሲቀጠቀጥ ምልክቶችን ሊያሳይ ይችላል።

❶ • ጀርባን መውረር ማሳከክ፥ መመዝመዝ

❷ • እንደ ድንጋይ መክበድና ስሜት አልባ መሆን

❸ • ልክ እንደ እሳት ማቃጠልና ንዳድ መብላት

❹ • አስቀድሞ ያልነበረ ሽፍታ ፣ ብጉር ፣ እብጠት ፣ ቁስል መውጣት

❺ • ቦታው ላይ ልክ ጸጉር የወጣበት ይመስል መጥቆርና ጥላሸት መልበስ

❻ መቁጠሪያ ሲያዩ ፍርሃት ፍርሃት ማለት፣ መጨነቅ፣ መቁጠሪያ ላለመጠቀም ከውስጥ የራስ አሳብ የሚመስል ድምፅ መወትወት ማከባበድ፥ ጉዳቱን አግዝፎ ማመንታት፥

እና ሌሎች ተመሳሳይ ምልክቶች ይታያሉ። እነዚህ ምልክቶች ሳትሰግዱና ሳትጸልዩ ዝም ብላችሁ ብትቀጠቅጡት አይታዩም።

ቅዱስ ቃሉ እንደዚህ ይለናል < የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ ልበሱ > አፌሶን 6፥10-18

t.me/abat_memhir_girma

